# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – glnlm @ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org 3ኛ ደብዳቤ 2005 እአአ 3rd Quarter 2005

**ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል። (ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13)**

## በስጦታ ማገልገል

ታላቅ ወንጌላዊ መሆን ምኞቴ ነው። በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች ሰብኬ፥ወደ ጌታ ሲመለሱ ማየት ሁልጊዜ አልማለሁ እውነቱ ግን እስከ ዛሬ ድረስ በእስታዲዮም እንድሰብክ የጋበዘኝ አላጋጠመኝም። ይሁን እንጂ፥የልቤ ምኞትና ፀሎቴ አሁንም ያው ነው። ምክንያቱም፡– ጌታ ኢየሱስን ለመከተል ያደረግሁት ውሳኔ፥ሕይወቴን እጅግ ስለ ለወጠና ዓለም ሁሉ እኔ የቀመስሁትን ቢቀምስ ደስ ስለሚለኝ ነው

ከአሥር ዓመታት በፊት መደበኛ ሥራዩን አቋርጬ ሙሉ ጊዜዩን ወደ አገልግሎት እንድወጣ ጌታ ልቤን አነሣሣ። እኔም በእሽታ ለመታዘዝ ወሰንሁ። ነገር ግን በምን አኳኋን እንደማገለግል በግልጽ አላወቀሁም ነበር። ኮምፒወተር ነክ አገልግሎት ሊሆን እንደሚችል ታሰቦኛል። ምክንያቱም ትምሕርቴ በዚያ ስለ ሆነ ነው። በዚያን ጊዜ፡– የመሥሪያ ቤቴን ዌብ ገጽ ገንብቼ ስለ ፈጸምሁ፥ አገልግሎቴንም በዚያው በዌብ ገጽ ግንባታ መጀመር እንዳለብኝ ተረዳሁ።

ወዲያውኑ የዌብ ገጽ ገንብቼ፥ጌታ ኢየሱስ እንዴት ሕይወቴን እንደ ለወጠ ጽፌ አወጣሁ። ከጥቂት ቀናት በኋላም ከግሪክ፥ አቴንስ ከተማ፥ ኢ–ደብዳቤ ደረሰኝ። አንድ የደኅንነቴን ታሪክ አንብቦ ልቡ የተነካ ሰው፥እንድፀልይለት ጠየቀኝ። ከዚያም፥ከሲያትል፡ዋሽንግተን፥ከሚምፊስ፡ቴኔሲና ከካይሮ መልክቶች ደረሱኝ።

የዌብ አገልግሎቴን በጀመርሁ በዓመቱ በወር 800 ጐብኚዎች፥ከ72ሐገሮች ጎብኝ ተውታል። ይህም ፈጣን ዕድገት ነው። እኔም፥ ተጨማሪ ምስክርነቶችንና መዝሙሮችን አወጣሁ። ሕዝቡን ወደ ጌታ ኢየሱስ እምነት የሚያነቃቁ የቪዲዮ መልክቶችን ጨምሬ አወጣሁ። ይህንን ያእንተርኔት አገልግሎት ከጀመርሁ ይኸው አሥር ዓመት ሆነ። በአካል በብዙ ሕዝብ ፊት ቆሜ የምሰብከው በብዛት አይደለም። ነገር ግን ወደ አምላኬ ጥሪ አቀጠጫ እየተራመድሁ መሆኔ ይታወቀኛል። በዚህ ዓመት መጀመሪያ፡– ከ150 ሐገሮች የመጡ፥አሥር ሺ ሰዎች፥የዌብ ገጽ አገልግሎቴን ጎብኝተዋል።

በዚህ የእንተርኔት አገልግሎት ብዙ ሰዎች በጌታ አምነዋል። የሚገርመው ግን ሁሉም የዳኑት በእኔ ብቻ ቃልና ምስክርነት ላለመሆኑ ነው። ለምሳሌ፡–አንዱ የቡድሓ ዕምነት ተከታይ ወደ ጌታ ኢየሱስ ዕምነት የመጣው፥ የአንዱን የቡድሓ አማኝ የነበረ ሰው ምስክርነት በማንበብ ነው፡ ከቺካጎ ኢሊኖይ ፡– አንዲት ሴት ጌታን የተቀበለችው፡–(በቻት ክፍል chat room) በአንዲት የፓስተር ሚስት ምስክርነት አማካኝነት ነበር። እንዲሁም ላትቪያ የተባለ ሐገር ሰው በኮምፒውተሩ ፊት ተንበርክኮ ጌታን የተቀበለው፡– ከቤቱ ውስጥ ሆኖ የወንጌሉን ቃል የሚያካፍልን ወንድም በእንተርኔት ቪዲዮ አይቶ ነበር። መልክቶቻቸውን ያስተላለፍሁላቸው አገልጋዮች፥ አንዳቸውም የኮምፒውተር ዕውቀት የላቸውም። የጌታ ኢየሱስን አዳኝነት የመስበክ ፍቅርና ጸጋ ግን አላቸው።

ቡድሐውን፥የቺካጎዋን ሴት ሆነች የላትቭያውን ሰው ወደ ጌታ የመራሁት በአሌ ቃል አይደለም። ሆኖም ብዙ ሰዎችን ወደ ጌታ የማምጣት ምኞቴንና ፀሎቴን አምላኬ አክብሮልኛል። ራሱ ባስተማረኝ በጽሕፈት፥በዌብ ገጽና በመሳሰሉት ችሎታዎቼ በመጠቀም ፥ ወንጌሉን ለመስበክ ስጦታ ባላቸው አገልጋዮች አማካኝነት የክብሩ መሣሪያ አድርጎኛል።

> **እግዚአብሔር ለብዙ ሰዎች የፍቅሩን ወንጌል የማድረስ ምኞቴንና ፀሎቴን አከበረልኝ።**

አሁንም ቢሆን፥ታላቅ ወንጌላዊ በመሆን ብዙ ሰዎችን ወደ ጌታ እየሱስ ማምጣት እመኛለሁ። ምናልባት አንተም እንደ እኔ ጌታን በአገልግሎት ለማክበር ትመኝ ይሆናል። ምናልባትም በምን እንደምታገለግል ርግጠኛ አይደለህም። ይህ ከሆነም፡– እስከ አሁን ጌታ ያስተማረህንና ያለማመደህን ተመልከት።(ምን ዕውቀት፥ምን ትምሕርትና ችሎታዎች አሉህ?) ከዚያም ችሎታዎችህን ለጌታ ክብር ለማዋል፡– ልብህን ምኞትህንና ፀሎትህን በዚያ አቀጣጫ አተኩር። ከዚያም ጌታ ልብህን ባነሣሣ መጠን በዕምነት ተነሣና ተራመድ። ቶሎ ባይሳካልህም ጨክነህ ቀጥልበት። የጽድቅ ሥራ ቀላል ሆኖ ስለማያውቅ ፈጥነህ ተሳፋ አትቁረጥ። ምክንያቱም ጥሪህን ሰምተህ በመታዘዝህ፡– ስንት ነፍሳት ወደ ጌታ እንደሚመጡ፥ስንት አማኞች ደግሞ በአገልግሎትህ እንደሚጽናኑ የሚያውቅ ጌታ ብቻ ነው። ከዓመታት በኋላ ግን በመታዘዝህ ጌታን ታመሰግናለህ። (አይዞህ፥በርታ፥ ተነሣና በውስጥህ ባለህ ማንኛውም ጸጋ ጌታህን አገልግል። ታማኝነትን ካየብህ፡– ጌታ በአዲስ ቀባት፥ለአዲስ አገልግሎት ሊሾምህ ምክንያት ያገኝብሃል።

(ኤሪክ ኤልደር የተባለ ወንድም ምስክርነት)

“መከሩ ብዙ ነው፥ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት” ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ፤ ማቴዎስ 9፥37–38)

### ከእግዚአብሔር ፍቅር
**ወንጌላዊ የደብዳቤ መልዕክት አገልግሎት**
*God's Love Gospel Newsletter Ministry*

ተወዳጅ ወገኖች፡– በስጦታ ስለ ማገልገል÷ከላይ ያነበባችሁትን ምስክርነት ሳዘጋጅ ስለዚሁ የደብዳቤ አገልግሎታችን መመስከር ጠቃሚ ሆኖ ታሰበኝ። ስለ አጀማመራችን በጥር 1994 ዓም ደብዳቤ አችን (September 2002) መስክሬ የነበረውን እደግማለሁ። ከዚያ ወዲህም ጌታ የት እንዳደረሰን ብመሰክር ለጌታ ክብር መልካም ነው።

ከ1996 ገደማ ጀምሮ ጌታ በታላቅ መንፈሳዊ ተሐድሶ ውስጥ አገባኝ። ቤተሰባችን በመንፈስ ቅዱስ እሳት እየተቀጣጠለ÷ የጌታ ኢየሱስን ፍቅር ለሁሉ ለማሰማት እጠማ ነበር። ራሴንም ለይቼ በመቀደስ መብራቴን ለማሳየት ወሰንሁ።

በዚሁ በጋለ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ውስጥ እያለን በ1998 ዓም እአአ በምሠራበት ፋብሪካ አብረውኝ የሚሠሩትን የመኪና ዕቃ ማምረቻ ሠራተኞች በወንጌል የመድረስ ሸክም ተሰማኝ። ወድያውም My God Love's You በሚል የአንድ ገጽ መልዕክት በእንግሊዝኛ በማዘጋጀት ማሰራጨት ጀመሁ። በሥፍራው የነበሩ ጥቂት አማኞች በታላቅ ደስታ በማሰራጨቱ ስለ ተባበሩ በሦስቱም ፈረቃዎች ሰፊ ተነባቢነት አገኘን፤ ሰዎችም ጌታን ተቀበሉ፤ጌታ ስሙ ይክበር። ተዳክመው ከቤተ ክርስቲያን ርቀው የነበሩ አማኞችም በርትተው ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱ ምክንያት ስንሆን አየን። በዚህ የተጋን ጥቂቶችም የመሥሪያ ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሳምንታዊ ስብሰባ ጀመርን።

በዚህ ውጤት በመደነቅ እያለሁ ነበር ጌታ ይህንን የምታነቡትን አገልግሎት ወደ ልቤ ያመጣው። ከእግዚአብሔር ፍቅር ያልነው የዚህ ደብዳቤ ስምም የተወሰደው My God Love's You ከሚለው ጌታ ሲሠራበት ካየነው ስም ላለመራቅ የተመረጠ ነው። ለነገሩ እንጂ ከእግዚአብሔር ፍቅር የተሻለ ስም ይገኛል?

እአአ በ1999 በአቀራረቡ ምንም ያህል ብስለት ያልነበረው የአማርኛ መልክት በካንሳስ ከተማና አካባቢው በማሰራጨት የዕምነት ርምጃ ጀመርን። ከዚያም ከሰሜን አሜሪካ አድራሻዎችን በመሰብሰብ አሰራጨን። ብዙም ሳይቆይ አውሮጳና አፍሪካ÷ እንዲሁም መካከለኛ ምሥራቅ መድረስ ቻልን። በአሁኑ ጊዜ ወገኖች በስልክ÷በኢ–ደብዳቤና በካርድ ድጋፋቸውንና ምስጋቸውን በመግለጽ ያበረታቱናል፤እግዚአብሔር ይመስገን። ድካማችንም በከንቱ እንዳልሆነ ቅዱሳንና መንፈስ ቅዱስ እያረጋገጡልን ስለ ሆኑ ክብርንና ምሥጋናውን ለባለቤቱ ለጌታ እየሱስ እንሰጣለን። ቅዱሳንና መንግሥቱን ለማገልገል የማንበቃውን ሊጠቀምብን በመፍቀዱ በታላቅ አክብሮት እንታዘዝለታለን። በአገልግሎታችን አንድም ሰው ወደ ጌታ ቢመጣና ÷ አንድም ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ውጊያው ቢጽናና ደስታችን ሙሉ ይሆናል። እኛ ብቻ ታማኞች እንሁን እንጂ ጌታስ መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥም፤ ስሙ ይክበር።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ጌታ በቅዱሳን ምክርና ማደፋፈር ልባችንን አነሣስቶ የሚያስፈልገውንም አዘጋጅቶልን፡– ይህንኑ አገልግሎት በዘመኑ መሣሪያ በእንተርኔት ማቅረብ ጀመርን። ይኸውም ሁለተኛ ዓመቱን የያዘው www.ethioGodslove.org የእንተርኔት አገልግሎታችን ጌታን እጅግ የምናመሰግንበት ግሩም ስኬት አሳይቶአል፤ ክብር ለጌታ እየሱስ ይሁን። ለምሳሌ በታሕሣስ 2004 በቀን 31 ሰዎች÷ በወር 987 ሰዎች ከመላው ዓለም የጎበኙን ሲሆን ባለፈው መጋቢት March 2005 ደግሞ 1164 ሰዎች ገጻችንን ጎብኝተዋል።

www.ethioGodslove.org በአሁኑ ወቅት ጽሑፍ የሚነበብበት ብቻ ሳይሆን÷ምርጥ መዝሙሮችም የሚደመጡበት ነፃ አገልግሎት ስለ ሆነ÷የብዙ ስደተኛ ወገናችን ማረፊያና መጽናኛ ሥፍራ ሆኖአል ክብርና ምሥጋና ለእግዚአብሔር ይሁን

ስለዚህ ወገኔ ሆይ:- የጌታህን የየሱስ ክርስቶስን መንግሥት ለማገልገል ያለህን ምኞትና ፀሎት አታቋርጥ:: ጌታ በልብህ ውስጥ የሚያመጣቸው ራዕዮች በመጀመሪያው ቅዠት መምሰላቸው አያስደንግጥህ:: አንዳንድ ጊዜ ፈጽሞ ባልተለመዱ መንገዶች እንድናገለግለው ጌታ ይጠይቀናል:: ስለዚህ ራዕይህ እንግዳ ቢመስል ከጌታ አይደለም ብለህ አትጣለው:: የሰዎችና የሴይጣን ተስፋ ማስቆረጥም አዲስ ነገር አይሁንብህ:: ጌታን እንኳ ከጥሪው ሊያስቀሩት ሞክረዋል:: ጨክነህ መራመድ ስትጀምር ታመልጣለህ:: ጌታም እንዳሰበው ይከብርብሃል:: አሜን? ጌታ ሳይመጣ መክሊትህ ብዙ ያፍራልህ:: ለሕዝብህ በረከትና ለጌታህ ክብር ያብቃህ:: አሜን? አዎን፤ አሜን::



# አታመንዝር

(ኦሪት ዘጸአት 20 ÷ 14)

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በውስጡ የሚገኙትን ሁሉ በዕውቀትና በታላቅ ጥበቡ መፍጠሩን እናውቃለን:: የተፈጠሩትም ሁሉ በተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት እንዲኖሩ ሆነው ተፈጠሩ:: ከሥነፍጥረት (ባዮሎጂ)÷ከንጥረ ነገር (ኬሚካልና) ከሕብረተሰብ÷ አንድም ያለ ሥርዓት ለመኖር የተፈጠረ የለም:: ሊኖርም አይችልም:: ከዋክብት በሰማይ ላይ÷ሕዋሳት በአካል ውስጥ÷ ንጥረ ነገር በኮምፓውንድ ውስጥ ÷ እንዲሁም ግለሰብ በሕብረሰብ መኻከል ያለ ሕግና ሥርዓት ሊኖር አይችልም:: እግዚአብሔር ሕግን የሰጠን÷ ሥርዓትንም ያስተማረን ለዚህ ነው:: እንድንገዛትና እንድንበዛባት የተሰጠችንን ምድሪቱን አጥፍተን ራሳችንም እንዳንጠፋ ነው::

አሥርቱ ትዕዛዛት ለሰው ልጅ ከተሰጡ ትዕዛዛት ሁሉ ዋነኞቹ ናቸው:: ከአሥሩም አንዱ "አታመንዝር" የሚለው አብዛኛው ሰው የሚያውቀው ነው:: በኢየሱስ የማያምንና በትምሕርቱ የማይገዛ ሁሉ በአመጻ ይኖራል:: አመጸኛውን ሰው ሕግ እንዲያከብር አንጠይቅም:: ሕግን ከማክበር በፊት በልጁ በማመን ወደ መንግሥቱ መግባት ይቀድማልና::

በዚህ ጽሑፍ ልንመለከት የተነሣሣነው ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የኃጢአታቸውን ይቅርታ ከተቀበሉ በኋላ ተመልሰው በማመንዝር የሚበድሉትን ነው::

ማመንዝር የሚለውን ቃል ትክክለኛ ትርጉም ለመረዳት adultery የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ትርጉም ተመለከትኩ እርሱም (ባለትዳር ሆነው እያሉ÷ከትዳር ውጭ ግብረ ሥጋ ማድረግ) እንደ ሆነ ይገልጻል:: እግዚአብሔር ግን አታመንዝር ይላል:: በሚከተለው ክፍል ከዚህ ክፉ በሽታ ለመጠበቅ ወይም ለመዳን የሚረዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃሳቦችን እና ቀርባለን::

## ማመንዝር ከየት ይጀምራል?

ከዓይንና ከልብ:- "አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል::" (የማቴዎስ ወንጌል 5÷27-28)

ስለዚህ ማመንዝር ተግባራዊ ሆኖ ከመፈጸሙ በፊት እንዳፈቀደው የሚዞር ዓይን አምጥቶ በልብ ውስጥ ሀሳቡን ያበቅላል:: በፍጥነት በፀሎትና በንስሐ ያልተቋቋሙትም ሀሳብ ውሎ ሲያድር ወደ ተግባር ይተረጎማል:: የአንተ ዓይን እንዴት ነው? በሀሳብህ ምን ታዘወትራለህ? አንቺስ?

**አለመታረቅ** :- በመጠኑ ይለያይ እንጂ ግጭት የሌለው ትዳር አይገኝም:: ነገር ግን ባለ ትዳሮች በየጊዜው በመወያየት ቅራኔዎቻቸውን እየፈቱ ካልሄዱ እያደር የልብ መራራቅንና የባሰንም ነገር ያስከትላል:: ስለዚህ ባል ለሚስቱ÷ ሚስትም ለባልዋ የልባቸውን ሁኔታና ፍላጎት መገላለጽ አለባቸው:: ቅራኔአቸውን ሁለቱ ተነጋግረው በመፍታት ፈንታ ወደ ሌላ ሰው በመሄድና በማማት መጽናናት ቢሞክሩ ግን ውጤቱ አደገኛ ነው:: በተለይም አጽናኙ ተቃራኒ ፆታ ከሆነ÷አደጋው የማመንዝር ኃጢአት ሊሆን ይችላል::

**አለመብሰል**:-አብዛኛው ሰው ትዳር ውስጥ የሚገባው÷የትዳርን ትርጉም ሳይረዳ ነው:: ስለዚህም አንዱ ሌላኛውን ለማገልገል ሳይሆን እያንዳንዱ በሌላኛው ለመገልገል ተዘጋጅቶ ነው የሚቀርበው:: በቆራጥ ታማኝነትና በቃል ኪዳን ፋንታ ፍቅር መሰል ስሜተኛነት ይዘወተራል:: ዕውነተኛ ፍቅር ግን ውሳኔ እንጂ የስሜት ጉዳይ አይደለም:: ለማፍቀር ውሳኔ ያደረገ ሰው ቢሰማውም ባይሰማውም ቃል ኪዳኑን ያከብራል:: አመንዝራነት ግን ክህደት ስለ ሆነ ቃል ኪዳኑን የማይረሳ ሰው ለትዳሩ የታመነ ነው::

**መጥፎ አርአያ**:-የዚህ ዘመን የሕብረተሰቡ አስተማሪ ቴሌቪዥን ሆኖአል ቢባል ከዕውነት የራቀ አይደለም:: በቴሌቪዥን ስለ ትዳርና ስለ ፍቅር ምን እንደሚተላለፍ ስንመለከት የዚህ ዓለም ሁኔታ እያሽቆለቆለ የሚሄድበትን ምክንያት ማስተዋል አይሳነንም:: በቴሌቪዥን ጨርሶ እንከን የለሌው የሚመስል ትዳር÷ይታያል::ተግባራዊነቱ ከቲያትር መድረክ የማያልፍ ፍቅር መሰል የመድረክ ጨዋታ በቲቪ ዘወትር እናያለን:: ከዚያም ያ የቲቪ ቅዠት በትዳራችን ሳይታይ ሲቀር ችግር ያለን ይመስለንና ጠብ እንከፍታለን:: ወይም በቲቪ ላይ ያየነውን ትርዒት ሊያጫውተን የሚችል ለማግኘት ስንል በማመንዝር ኃጢአት ውስጥ እንዘፈቃለን:: ዕውነተኛው ትዳር በቤታችን ያለው ሆኖ እያለ÷ የተዋኒያንን ጨዋታ እንደ ዕውነት በመቁጠር ትዳራችንን እንራገጣለን:: ጌታንም እግዚአብሔርን እንበድላለን::

**እርካታ**:- የማመንዝር ዋና መንስኤ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የእርካታ ፍላጎት ነው:: የሰው ሁሉ ዕውነተኛ እርካታ የሚገኘው እግዚአብሔርን ቀርቦ በማወቅና በመከተል ብቻ ነው:: ስለዚህ ሊያረካው ለሚችለው ለእግዚአብሔር ያልተሰጠውን ነፍስ ሊያረካ የሚችል ባል ሆነ ሚስት የትም አይገኝም:: ስለዚህ "ላም ካልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንደሚሄድ ሰው ውጤቱ ተስፋ መቁረጥና ሌላ ለመሞከር ወደ መነሣት (ወደ ማመንዝር) ወይም ወደ መፋታት ይመራል::

**እንክብካቤ**:- ትዳር እንደ ዕጽዋት ነው:: ገበሬ ዘሩን እንደሚመርጥ፡ የትዳርም ጓደኛ በጥንቃቄና በፀሎት÷በጥበብና በማስተዋል ይመረጣል:: በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የተደረገ ምርጫ ደግሞ የእግዚአብሔር ጥበቃ ዋስትና አለው::ከተገኘም በኋላ በአግባቡ ተተክሎ ብዙ እንክብካቤ እንደሚደረግለት አትክልት፡ መንከባከብ ያስፈልጋል:: የሥጋም ሆነ የሕሊና እንክብካቤ የጎደለው ትዳር ለማመንዝር ኃጢአት የተጋለጠ ነው:: ስለዚህ የትዳር ጓደኛን እንክብካቤ መንፈግ ውጤቱ ፈጽሞ አያምርም::

ሰው ሰውን ሲያፈቅርና ሲያገለግል ከማየት የበለጠ እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ምንም የለም:: ሰውን ማገልገል ደግሞ ከሁሉ በሚቀርበን በትዳር ጓደኛችን መጀመር ይኖርበታል:: ባለቤትህን ባለማፍቀርና ባለመንከባከብ ትዳርህን በድለህ ከሆነ:- ተስፋ አትቁረጥ፤ ይህ አለማስተዋል በብዙ ቤት ያለ ነው:: አመንዝራዊ ሃሳቦችን በአእምሮ ውስጥ በማስተናገድ ራሳቸውን በብዙ ፈተና ውስጥ የጣሉ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ:: ነገር ግን ትዳሮች እንዲጨናገፉ ወይም በረከት እንዲጎድላቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: ስለዚህ ንስሐ በመግባትና ቃል ኪዳንን በማደስ ቤተሰብንና ትዳርን እንደገና እንድናንፅ እግዚአብሔር ይጠራናል:: የተሰጠንንም ውድ ነገር በቸልታ እንዳንይዝ ይቀሰቅሰናል::

**መናዘዝ**:- እግዚአብሔር በቃሉ እየተናገረና በመንፈሱ እያሳሰበህ በፊቱ በአመጻ የተመላለስህበትን ኃጢአት በመናዘዝ ከልብ መጸጸትህን ግለጽለት:: በቃሉ አታመንዝር ካለው ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ምንም መከራከር ተስማማ ::

**ንስሐ መግባት**:- በተናዘዝከው ጉዳይ ንስሐ ግባ:: የምታውቀው ኃጢአት ካለ:- ዛሬውኑ ማቋረጥ አለብህ/ሽ:: ካልሆነ ግን ንስሐ እየገቡ ኃጢአትን አለማቋረጥ በራስ ከመቀለድ አልፎ የእግዚአብሔርንም ቁጣ መጋበዝ ይሆናል:: ወደ ንስሐ እስክትመጣ ድረስ የታገሰህ ጌታ አሳልፎ ከሰጠህ አወዳደቅህ የከፋ ይሆናል:: አንቺም::

**ምሕረቱን መቀበል**:- ከተናዘዝህና ንስሐ ከገባህ በኋላ ወደ ኃጢአትህ እንዳትመለስ በራስህ ችሎታ አትደገፍ፤ እግዚአብሔር በቅድስና እንድትኖር ሊረዳህ እንደሚችልና እንደሚፈልግም አምነህ በእርሱ ታመን::መንፈስ ቅዱስን እያዳመጥህ በአክብሮት ተከተለው::

**ግንኙነትን ማቋረጥ**:- ለማመንዝር ውድቀት ያደረሰህን ማንኛውንም ወዳጅነትና ግንኙነት አሁን አቋርጥ ! ! ከሳምንት በኋላ ÷ ወይም በሚቀጥለው ቀን እንኳ ሳይሆን አሁን አቁመው:: ምክንያቱም ይህንን ዓይነት የጠላት ሥራ መቁረጥ የሚቻለው አሁን በመቁረጥ ብቻ ነው:: አረም ሁሉ ካደረ ሥር ይሰዳል:: ከአሁን ጀምረህ በስልክ÷ በደብዳቤ ሆነ በመገናኘት÷ ምንም ዓይነት ንግግር ከዚህ/ች ሰው ጋር አይኑርህ/ሽ::

**ምሥጋና** :- ሊሞት የተዘጋጀውን ወይም ጠላት ያደባበትን ትዳርህን መልሶ ያበጅልህ ዘንድ የፈቀደውንና የሚችለውን እግዚአሔር አምላክህን አመስግን

**ቃል ኪዳንን ማደስ**:-ጤነኛ ትዳር በብዙ ድካም ይጠበቃል:: ቁስለኛው ትዳር ደግሞ የበለጠ ድካምና ጥረት እንደሚጠይቅ መገመት አያዳግትም:: ስለዚህ ንፁሕና ሰላማዊ ትዳርን ለመገንባት ዛሬውኑ ተነሣ:: እግዚአብሔርም ያከናውንልሃል:: አሜን ?



አሜን::

# እየሱስ

## ከሰው የተወለደ አምላክ

"እየሱስም ... ደቀ መዛሙርቱን ፦ ሰዎች የሰውን ልጅ (ኢየሱስን) ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ።"
(ማቴ 16 ፥13)

ብዙ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ኢየሱስ ታላቅና ምስጉን መሪ መሆኑን ያምናሉ፡ ነገር ግን አንዳንድ ያልተረዱ ክርስቲያኖችም እንኳ ሳይቀር፥ጌታ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ርግጠኛ አይደሉም።ይህም እጅግ የሚያሳዝን ነው። ይህንን አስመልክቶ ሲ ኤስ ሉዊስ የተባለው መምሕር "ኢየሱስ ክርስቶስ፦ ጌታና አምላክ ካል ሆነ፥ ዕብድ ወይም ሐሰተኛ መሆን አለበት። ነገር ግን አምላክነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እጅግ ብዙ ነው" ብሏል።

### በስመ አብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ የምታምኑ ሁሉ፦ ሰላሙ ይብዛላችሁ።

የክርስትናችን ዋና ማዕከል የሆነውን የጌታችንን የእየሱስ ክርስቶስን ሰውና አምላክ መሆን በእርግጠኝነት እንድታውቁ መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚለውን በጸሎት እንድትመለከቱ በእግዚአብሔር ፍቅር እንጋብዛችኋለን። የማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ብትሆኑ፥መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ገልጣችሁ ተመልከቱ።

---

መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 1፥1-14 የሚለውን እስቲ እንመልከት፦ "በመጀመሪያው ቃል ነበረ ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። ... ቃልም ሥጋ ሆነ ፡ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ..."

ወገኖቼ፦ በየዘመኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በመጻረር የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚክዱ ታይተዋል። ክርቲያን ነን ከሚሉትም እንኳ ሳይቀር ጌታ ጥሩ መምሕር፥ መልካም መሪ ፥ ታላቅ ሰው መሆኑን የሚቀበሉ ፦ ነገር ግን ፈጣሪና አምላክ መሆኑን ያልተረዱ ወይም የሚክዱ አሉ። የመጽሐፍ ቅዱስን ዕውነት ለምናምን ለእኛ ግን ማስረጃችን ብዙና የታመነ ነው። የሚከተሉትን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ባሕሪያት ተመልከቱ፦

## ዘላለማዊነቱ

### እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደ መሆኑ መጠን፥እየሱስ ዘላለማዊ ነው።

"ሕፃን ተወልዶልናልና ፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም ድንቅ መካር፥ኃያል አምላክ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤..."
ትንቢተ ኢሳይያስ 9፥6-7

"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።"
ወደ ዕብራውያን 13፥8

"እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፡ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል ... ትርጓሜውም ፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው ።
የማቴዎስ ወንጌል 1፥23

"...ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፦ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፦ ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር፥ ውዳሴ፥ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።
ዮሐንስ ራዕይ 4፥11

"በሰማይና በምድርም ከምደርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእርሱ ውስጥ ያለ ሁሉ፦ በረከትና ክብር ምሥጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ። (ዮሐንስ ራዕይ 5፥13)

## እየሱስ ፈጣሪ ነው

### እግዚአብሔር አምላክ እንደ መሆኑ እየሱስ ፈጣሪ አምላክ ነው።

"እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና፡ ..."
(ቆላስይስ 1፥15-16)

"... በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።"
(ዮሐንስ ወንጌል 1፥3)

## አምላክነቱ

"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን ፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕሪዩ ምሳሌ ሆኖ፥ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ ..."
(ዕብራውያን 1፥1-3)

## ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣኑ

"እነሆም በአልጋ የተኛ ሽባ ወደ እርሱ አመጡ። እየሱስም ዕምነታቸውን አይቶ ሽባውን፦ አንተ ልጅ፥ አይዞህ፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ፡ አለው። ... ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአትን ያስተሰርይ ዘንድ የሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፥..." (ማቴዎስ ወንጌል 9፥2-6)

## በዓለም ላይ የሚፈርድ አምላክ

"ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም።ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።"
(የዮሐንስ ወንጌል 5፥22-24)

እንዲሁም አማኑኤል፥ ሕያው ቃል (Logos) የእግዚአብሔር ልጅና የሰው ልጅ፥ ጌታና አምላክ የሚሉት መጠሪያዎቹ በትንቢት ለተነገረለት ለመሢሕ የተመደቡ ስሞቹ ናቸው።

## ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው

"ግን እርሱ የዕውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ ዕውነት ሁሉ ይመራችኋል ፤ ... የሚመጣውንም ይነግራችኋል። እርሱ ያከብረኛል፥ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና። ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው፤ ስለዚህ ፦ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ።" (የዮሐንስ ወንጌል 16፥13-15)
"... የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው፡ የአንተውም የእኔ ነው።..."
(የዮሐንስ ወንጌል 17፥10)

## እየሱስ፦አምላክ ሰው ሆነ እንጂ

### ሰው ምላክ አልሆነም

እየሱስ፦ "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ አልቈጠረውም፥ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።" (ፊልጵስዩስ 2፥6-8)

## ጌታ እየሱስ፦ የሚመለክ አምላክ

ጌታ እየሱስ ራሱ በማቴዎስ ወንጌል 4፥10 እንደ ተናገረው ሰው መስገድ ያለበት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ጌታ ኢየሱስ የሚሰገድለት አምላክ ነው።

"በታንኳዪቱም የነበሩት ፦ በዕውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት።" (የማቴዎስ ወንጌል 14፥33)

## ጌታ እየሱስ ራሱ አምላክነቱን ይገልጽ ነበር

"እኔና አብ አንድ ነን።" (የዮሐንስ ወንጌል 10፥30) "እየሱስም፦ ዕውነት ዕውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው" (የዮሐንስ ወንጌል 8፥58)

## ጌታ ሙሉ ሰውና ሙሉ አምላክ ነው

"እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ አልቈጠረውም፥ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።" (ፊልጵስዩስ 2፥ 6-8)

"... ስለ ልጁ ግን፦ አምላክ ሆይ፥ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግ

ሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው:: … ይላል" (ዕብራውያን 1÷8)

"እኔና አብ አንድ ነን::"
(የዮሐንስ ወንጌል 10÷30)

"ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ:- አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል::" (ዮሐ/ ራዕይ 1÷8)

# እየሱስ ምንም ኃጢአት አልሠራም

"በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካሕናት የለንምና፤ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካሕናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኃጢአት አልሠራም::" ዕብራውያን 4÷15 አ/መ/ት)

# በእየሱስ የሚታመን መንግሥተ ሰማይ ይወርሳል

ክርስትናን ከሌሎች ኃይማኖቶች ልዩ የሚያደርገው ኢየሱስ ራሱ ነው:: የኃይማኖት መሪዎች መንገድ ያሉትን አመለከቱ:: ኢየሱስ ግን ራሱ የመዳን መንገድ ነው:: "ኢየሱስም :- እኔ መንገድና ዕውነት ሕይወትም ነኝ: በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም::" አለ::
የዮሐንስ ወንጌል 14÷6

"ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም: የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ::
1ዮሐንስ መልክት 5÷12-13

"… በክርስቶስም ትምሕርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤በክርስቶስ ትምሕርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት::"
2 ዮሐንስ መልክት 1÷9

ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ ለመውረስ:-

1ኛ:- የደኅንነትን ተስፋ በጌታ እየሱስ ብቻ ላይ አድርጎ በመታመን:- የእግዚአብሔርን ፍቅር መቀበል ግድ ነው:: ምክንያቱም

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::"
ዮሐንስ ወንጌል 3÷16

2ኛ:- ኃጢአተኛ በመሆንህ ተስማማ:-

"ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል÷በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም÷አንድ ስንኳ የለም::"
ወደ ሮሜ ሰዎች 3÷11-12

3ኛ:- ስለ ደኅንነትህ በግልጽ ጸልይ:-

"የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና"
ወደ ሮሜ ሰዎች 10÷13

4ኛ:- ጌታ እየሱስ አዳኝህ መሆኑን አምነህ በመቀበል ÷ የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን ተቀበል:-

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን÷በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው::" ይላልና:: የዮሐንስ ወንጌል 1÷12

5ኛ:- እየሱስ ጌታ መሆኑን መስክር:-

"እየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና"
ወደ ሮሜ ሰዎች 10÷9

ይህ መልዕክት ልብህን ከነካ በጌታ ፊት ተንበርክከህ ከልብ ጸልይ:: የሞተልህና ሞትንም ድል ነሥቶ ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ቀኝ ከፍ ያለልህን እየሱስን ተቀበል:: እርሱም ወደ አባቱ መንግሥት ይቀበልሃል:: ኃጢአትህም አይታሰብም የዘላለም ጥፋትም አያገኝህም:: እግዚአብሔር ይመስገን::

# ዝንጉ ሰው

*ዝንጉ በስንፍናው በምድር ላይ ተንጋልሎ*
*ነፍሱን ሲአል አፋፍ አመቻችቶ ጥሎ*

*እሳትን በመጉረስ ለእሳት የሚዘጋጅ*
*እንኳንስ ለሰማይ ለምድርም የማይበጅ*

*ሰላምና ደስታን ይሰጠኛል ብሎ*
*ዘላለምም ለእሳት አሁንም ቃጠሎ*

*ፍርድ አይቀርምና ይህ ዘመን ሲያበቃ*
*አንተ የምትተኛ ጊዜው ሳለ ንቃ !!!*



"ዓለሜን ማየት አለብኝ:: ገና ሰው ያየውን ነገር ስላላየሁ አሁን እግዚአብሔርን መከተል አልችልም:: በዓለም ላይ ብዙ ሳልደስት እንደ ጴንጤዎች:የመነኩሴ ሕይወት ውስጥ መግባት አልፈልግም:" መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- "አንተ የምትተኛ ንቃ÷ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል::
(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5÷14)

ዝንጉ ማን ነው? ሰነፍስ ማን ነው? የሰማይ አባቱን የፍቅር ጥሪ ችላ የሚል አይደለምን?በምድር ከፈተኛው ሥፍራ ላይ ወጥቶ ÷ በገደል አፋፍ ተንጋልሎ እግዚአብሔርን መከተል አምቢ የሚልስ ማን ነው?

"እኔ ሕያው ነኝ÷ይላል ጌታ÷ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል መላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና:: እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን::" (ወደ ሮሜ ሰዎች 14÷11-12)

እኔ እኮ በእግዚአብሔር አምናለሁ:: ሲበዛ አልወድም እንጂ ÷ በየበዓላቱ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ::

"እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤መልካም ታደርጋለህ፤አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ፤ ይንቀጠቀጡማል::
(የያዕቆብ መልእክት 2÷19)

እኔ ጥሩ ሰው ነኝ:: ካልነኩኝ በስተቀር ሰው አልነካም:: እንዲያውም ለሰው ጥሩ መሥራት እወዳለሁ:: ስለዚህ አምላክ ወደ ሲያል የሚሰድደኝ አይመስለኝም::

"ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ሁሉ ተሳስተዋል÷ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም÷አንድ ስንኳ የለም::"
(ወደ ሮሜ ሰዎች 3÷11-12)

እኔ ብዙ እቅድና ዓላማ ስላለኝ ለኃይማኖት ጊዜ የለኝም:: ሥራ ሠርቼ ብዙ ገንዘብ አፍርቼ÷በዚህ ምድር ላይ እንዲመቸኝ እፈልጋለሁ:: ከመልከ መልካሞች ጋር መደሰት እፈልጋለሁ:: ይህ ደግሞ ከመንግሥተ ሰማይ አያግድም::

"ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን?አታሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም::"
(1ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6÷9-10)

እኔ ኃይማኖተኛ ሰው ነኝ:: ከቤተ ክርስቲያን አልቀርም:: ካመቸኝም እጾማለሁ በድሃ አልጨክንም::ካመቸኝም አሥራት እንኳ እሰጣለሁ:: መንግሥተ ሰማይ እኔ ካልገባሁ ማን ይገባል?

"የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ÷ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም :: የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና::"
(ወደ ሮሜ ሰዎች 10÷3-4)

ውድ ወገን :- በነብያት ዘመን እንደ ነበረ ዛሬም÷ "ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች ፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች::እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ÷ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤እምቢ ብትሉ ግን ብታምፁም ሰይፍ ይበላችኋል ፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህንን ተናግሮአልና::"
(ትንቢተ ኢሳይያስ 1÷18-20)

የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ነው:: እርሱም ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ የሚቀበሉትን የሚያድን ስጦታ ሰጠ:: ያም ስጦታ አንድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው: ኢየሱስ ኃጢአትህንም ይቅር ሊልህ÷መንግሥተ ሰማይ ወራሽነትንም ሊሰጥህ ይችላል:: መጽሐፍ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን ÷ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው::" ይላልና ::
(የዮሐንስ ወንጌል 1÷12)

**የንስሐ ፀሎት**:- እግዚአብሔር ሆይ÷ ተግሳጽህን እሰማለሁ:: በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአቴ የተሰጠውን ልጅህን ኢየሱስን አምኜ በትምሕርቱ ለመኖር እቀበላለሁ:: አንተም በመንግሥትህ ተቀበለኝ:: አሜን::

ይህንን ፀሎት ከልብ ከፀለይህ÷ለምታገኛቸው ሰዎች ተናገር:: መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ:: በዕምነት እንድታድግ ከሌሎች አማኞች ጋር ሕብረት አድርግ::

(መጀመሪያ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሐምሌ 1993 ዓም God's Love, July 2001 ከተሰራጨ ደብዳቤ በድጋሚ የቀረበ)

## እየሱስ ጌታ ነው::
## ጌታ ይባርክህ::